# አሁን የፊት ጭምብል ማድረጊያ ወቅት ነው




**የመኸር/የክረምት ወቅት የመተንፈሻ አካል ቫይረስ ወቅት እየመጣ ነው!** የቺት ጭምብል ማድረግ ለሁሉም በCOVID-19 የመያዝ ከፍተኛ ስጋት ላለባቸው ሰዎችና ለቤተሰብ አባላቶቻቸው ይመከራል፡፡ በርግጥ ለሁሉም ሰው አሁን በቤት ውስጥ ህዝብ በሚሰበሰብባቸው ቦታዎች በሚሆንበት ወቅት የፊት ጭምብል ለማድረግ ጥሩ ጊዜ ነው፡፡

## ምን አይነት የፊት ጭምብል መልበስ አለብኝ?

- N95/KN95/KF94 የፊት ጭምብሎች በጥሩ ሁኔታ ይከላከላሉ፡፡
- የፊት ጭምብሎች አፍንጫ፣ አፍና አገጭን በአግባቡ መሸፈን አለባቸው፡፡
- እድሜያቸው ከ2 ዓመት በታች የሆኑ ህጻናት የፊት ጭምብሎች መልበስ የለባቸውም እንዲሁም ማንም ሰው ሲተኛ የፊት ጭምብል መልበስ የለበትም፡፡

## የአላሜዳ ካውንቲ ከሚከተሉት በስተቀር የግዛት ጭምብል የማድረግ መመሪያዎችን ያከብራል:

- የተወሰኑ የጤና እንክብካቤ ተቋማት ሰራተኞች ከታካሚዎች ጋር በሚገናኙበት ወቅት የፊት ጭምብሎች መልበስ ይጠበቅባቸዋል፡፡



## የፊት ጭምብሎች እንዴት ይሰራሉ?

የፊት ጭምብሎች ለባሹን እና በዙሪያው የሚገኙ ሰዎችን በCOVID-19 ከመያዝና በሽታውን ከማስተላለፍ ይከላከላሉ፡፡ የፊት ጭምብሎች በተጨማሪም እንደ ጉንፋን እና RSV ከመሳሰሉ የመተንፈሻ አካልን የሚያጠቁ ቫይረሶች ይከላከሉልዎታል፡፡



**ALAMEDA COUNTY HEALTH CARE SERVICES AGENCY**
**PUBLIC HEALTH DEPARTMENT**

ለተጨማሪ መረጃ:

[CDPH የፊት ጭምብል መቼ እንደሚለበስ]